# ያልተጻፉ ጥቅሶች

ጳውሎስ ፈቃዱ
paulosvictory@yahoo.com

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ተቆጥረው በተለያዩ ሰዎች የሚጠቀሱ "ያልተጻፉ ጥቅሶች" በየጊዜው ያጋጥሙኛል። "ዕርዱኝ ዕረዳችኋለሁ" ዐይነቶቹን ማለቴ አይደለም፤ ሌሎችን ወደ ውጭ ከማየት በፊት ራሳችንን ወደ ውስጥ መመልከት ብናስቀድም እመርጣለሁና። በመሆኑም ይህኛው ትኩረቴ በእኛው መካከል የሚዘወተሩ፣ በተለይም አገልጋዮቻችን ደጋግመው የሚሳሳቷቸውን ጥቂት ጥቅሶች ማሳየት ነው።

"የማይሠራ አይብላ" ወይም "ያልሠራ አይብላ" የሚለውን መጀመሪያ ባነሣው ደስ ይለኛል። ይህ "ጥቅስ" በመድረኮቻችን ተደጋግሞ ሲነገር እሰማለሁ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ግን አላገኘሁትም። ምን ማለት ይሆን?

መሥራት ያልቻለ ሰው መብላት የለበትም? ሕጻናት መብላት የለባቸውም? አረጋውያንስ? ዐቅመ ደካሞችስ ምን ይሁኑ? "ጥቅሱ" ለማንም ዕድል አይሰጥም። "ሥራ አጥ" ወይስ "ሥራ ፈላጊ" የሚለው ክርክር ውስጥ ለጊዜው ባልገባም፣ እነርሱም መብላት የለባቸውም እንደ ማለት ነው። አካል ጉዳተኞች እኩል ዕድል ከተሰጣቸው ከማንም ባልተናነሰ ሁኔታ መሥራት እንደሚችሉ አምናለሁ። የእነርሱም ጥያቄ ይኸው ነው - እኩል ዕድል። ነገር ግን መሥራት እንዲችሉ ማመቻቸት ቀርቶ፣ በራሳቸው ተፍጨርጭረው እንዳይሠሩ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ መተላለፊያውን ስንዘጋባቸው መገኘታችን የሚታይ እውነት ነው። እና መሥራት እንዳይችሉ ሆነው ሳለ መብላት የለባቸውም ማለት ነው? ለመሆኑ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ጭፍን ነውን?!

"ያልሠራ አይብላ" የሚለው የኮሚኒስቶች ጥቅስ ይሆን ይሆናል፤ በፍጹም ግን የእግዚአብሔር ቃል አይደለም! ከጥቁር አንበሳ ሆስፖታል ጀርባ "የኢትዮ ኩባ ወዳጅነት መታሰቢያ" ሀውልት ይገኛል። እዚያ መታሰቢያ ዘንድም የኮሎኔል መንግስቱ ኃ/ማርያምን ጨምሮ የ66ቱን አብዮት ታሪክ ቋሚ ማስታወሻ የሆኑ የተለያዩ ቅርጻ ቅርጾችን ማየት ይቻላል። በጊዜው ይደረጉ ስለነበሩት ሰላማዊ ሰልፎችና የዚያን ጊዜ መፈክሮች ማጥናት ከተፈለገም ተመራጭ ቦታ ነው። ከመፈክሮቹም መካከል "ያልሠራ አይብላ" የሚለው አንዱ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ሊሠራ የማይወድ አይብላ" ነው የሚለው (2ተሰ. 3÷10)። "ሊሠራ የማይወድ" እና "ያልሠራ (የማይሠራ)" በጣም ይለያያሉ። "ሊሠራ የማይወድ … አይብላ" የሚለው ሐረግ በቀጥታ የሚያያዘው መሥራት ካለመፈለግ ጋር ብቻ ነው፤ ትኩረቱ ሥራ ለመሥራት የመፈለግ ወይም ያለመፈለግ ጉዳይ ነው። ጥያቄው የልብ ነው፤ ለመሥራት የመፈለግ ጉዳይ ነው። መሥራት እየወደዱ መሥራት ያልቻሉ፣ ለመሥራት ዕድል ያላገኙ ሰዎች መብላት ይችላሉ። ስለዚህ ከላይ የዘረዘርናቸውን ሰዎች ከመብል የምንከለክልበት ምንም ዐይነት መሠረት አይኖርም። እንዲያውም እንደዚህ ዐይነት ሰዎችን መሰብሰብ፣ ማብላትና መርዳት የቤተ ክርስቲያን አንድ ኀላፊነት ነው። መሥራት እየቻለ መሥራት የማይወድ ሰው ከመብል ቢከለከል ግን ስሕተት አይሆንም።

"ሰዎች ሊያደርጉባችሁ የማትወዱትን ሁሉ እናንተም አታድርጉባቸው" የሚልም "ጥቅስ" ብዙ ጊዜ ሰምቻለሁ። ይህ ጥቅስ መጽሐፍ ቅዱስስ ላይ ይገኛልን? ምንስ ማለት ነው? በእርግጥ፣ እኛ ላይ እንዲደረግብን የማንፈልገውን ክፉ ነገር በሌሎች ሰዎች ላይ መፈጸም የለብንም። ለምሳሌ፣ ሰዎች ሲሰድቡን ደስ አይለንም፤ ስለዚህ መሳደብ የለብንም። የእኛ የሆነውን ነገር እንዲወስዱብንም አንፈልግምና እኛም የሌሎችን ንብረት መውሰድ አይኖርብንም። ሲመቱን፣ ሲጨቁኑን፣ ሲያሙን፣ ክብራችንን ሲነኩብን፣

መንገድ ሲዘጉብን ... ስለማንወድ፣ እኛም በተራችን በሌሎች ላይ እነዚህን እንዳንፈጽም ልንጠነቀቅ ግድ ነው።

ሰዎች ሁሉ በዚህ ወርቃማ ትእዛዝ መተዳደር ቢችሉ ሕይወት ምንኛ ውብ ትሆን ነበር! ይህ ጥሩ ምክር ነው፤ ምሉዕ ግን አይደለም። ክፉ አለማድረግ ብቻውን በቂ አይደለም፤ መልካም በማድረግ መታገዝ አለበት። ሲደረግብን የማንወደውን ነገር በሌሎች ላይ አለማድረግ መልካም ቢሆንም፣ ሲያደርጉልን የምንወደውን ነገር ለሌሎች ማድረግን ካላከልንበት ጎደሎ ይሆናል። ሰዎች እንዲያደርጉብን የማንወደውን ነገር አለማድረግ መልካም በማድረግ ካልታገዘ ወደ መሐል ሠፋሪነት (neutrality) ብቻ ነው የሚያመጣን፤ ክፉም መልካምም ሳይሆኑ እንዲሁ መሓል ላይ ተንሳፍፎ መቅረት ነው። ትኩስም ሆነ በራድ ባልሆነ ለብታ ልንመስለውም የምንችል ይመስለኛል። ይህ ምንባብ ግን ስለዚህ ጉዳይ ምንም አይናገርም፤ የጎዶሎነቱ መነሻም መጽሐፍ ቅዱስ ላይ አለመገኘቱ ነው።

የጌታ ኢየሱስ ንግግር ትክክለኛ ጥቅስ እንዲህ የሚል ነው፡- “እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው” (ማቴ. 7÷12፣ ሉቃ 6÷31)። ይህ ክፍል ክፉ አለማድረግን ብቻ ሳይሆን፣ መልካም ማድረግንም ይጨምራል። ሌሎች እንዲያደርጉብን የማንፈልገውን ባለማድረግ ሳንወሰን፣ እንዲደረግልን የምንፈልገውን ለሌሎች ማድረግንም ያስተምረናል። ክፉ አለማድረግ መልካም ማድረግን አይጨምርም፤ መልካም ማድረግ ግን ክፉ አለማድረግንም ያቅፋል። ጌታ ኢየሱስ መልካም አድራጊ ነው፤ ሐዋርያትም እንዲሁ። ስለዚህ እኛም ክፉ አለማድረግን ብቻ ሳይሆን፣ መልካም ማድረግም መመጨመር ይጠበቅብናል። የተሟላው የጌታ ኢየሱስ ትምህርት ይህ ነው።

በዚህ ትክክለኛ ጥቅስ መሠረት ከሆነ ባለመሳደብ ሳንገደብ፣ እንመርቃለን። ሰዎችን ባለመጥላት ብቻም አንወሰንም፤ መውደድንም እንጨምራለን። ውሸት አለመናገር ብቻ አይበቃንምና እውነትን እንናገራለን። የሰዎችን ንብረት አለመንካት ብቻ ሳይሆን፣ የራሳችንንም ለሌሎች እንሰጣለን።

“ሩጫዬን ጨርሻለሁ” የሚል ጥቅስም በየመቃብር ስፍራው ተጽፎ እመለከታለሁ፤ አንዳንዴማ በሕጻናትና ወጣቶች መቃብር ላይም ተጽፎ ይታያል። ሩጫውን ገና የጀመረና ለመጀመር እየተንደረደረ ያለ ሁሉ እንደ ጨረሰ መታሰቡ አስቂኝ ነው። ከዚህ የሚከፋው ግን “ጳውሎስ ‘ሩጫዬን ጨርሻለሁ’ ብሏል” እየተባልን የምንሰበከው ነገር ነው። እውነቱ ግን፣ ሐዋርያው ጳውሎስ በፍጹም እንዲህ አለማለቱ ነው። ለመሆኑስ ሐዋርያው ጳውሎስ የራሱን ጉዳይ ሲያሯሩጥ ነው እንዴ የኖረው? እርሱ ይህን የጻፈው እግዚአብሔር ሰጠውን ጥሪና ፈለግ ተከትሎ ለ30 ዓመት ከሮጠ በኋላ በመሆኑ ማንኛውንም ሩጫ ሳይሆን አንድን የታወቀ ሩጫ ነው የሮጠው። ስለዚህ ለልጁ ለጢሞቴዎስ “ሩጫውን (the race) ጨርሻለሁ” ብሎ ጻፈለት (2ጢሞ. 4÷7)።

እርሱ የሮጠው ማንኛውንም ሩጫ ወይም የራሱን የግል ሩጫ ሳይሆን፣ አንድን የታወቀ፣ በእግዚአብሔር የተወሰነና “መንገዱን (the Way)” ተከትሎ ያካሄደውን ሩጫ ነው። ባይሆን በአገልግሎት ስም የራሳቸውን ክብር፣ ስምና ቤት ሲገነቡና ለጥቅማቸው ብቻ ሲሯሩጡ የምናያቸው የእኛው ጉዶች “ሩጫዬን ጨርሻለሁ” ቢሉ ያስኬዳል። ያ የእግዚአብሔር ሰው ግን የሮጠው የራሱን ሪጫ ባለመሆኑ “ሩጫውን ጨርሻለሁ” ካለ በኋላ “... የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል። ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል” በማለት ተናግሯል። እኛስ?

“ነቢዩ ሙሴ አፈ ትብ ሰው ነበር ወይስ አፈ ትብ ሰው አልነበረም?” ብዬ የተለያዩ ሰዎችን ስጠይቅ፣ ሙሴ አፈ ትብ ሰው እንደ ነበር አስረግጠው ይነግሩኛል። ምን ያድርጉ? እኔም ብሆን እንዲህ እየተባለ በተደጋጋሚ ሲሰበክ ሰምቻለሁ። የስህተቱ መነሻ “ትብ” ማለት ከቃሉ ተቀራራቢነት የተነሣ “ተብታባ” የሚል ትርጓሜ ያለው ተደርጎ መወሰዱ ነው። ስለዚህ “ሙሴ አፈ ትብ ሰው ነበር” የሚል ያልተጻፈ ጥቅስ ያነብባሉ።

ሆኖም “ትብ” የሚለው ቃል የተገኘው ተባ ከሚለው ግስ ሲሆን፣ ትርጓሜውም “ሰላ፣ ተሞረደ፣ ቀለጠፈ (ለንግግር)” ማለት ነው፡፡ “የተባ ብዕር” እንደሚባለው ነው፡፡ [1] መጽሐፍ ቅዱስም እንደሚነግረን ከኾነ ሙሴ “ጌታ ሆይ፤ አፌ ኮልታፋ፣ ምላሴም ጸያፍ የሆነ ሰው ነኝ፤ … አፈ ትብ ሰው አይደለሁም” በማለት ነበር የተናገረው (ዘጸ. 4÷10)፡፡ “አፈ ትብ አይደለሁም” አለ እንጂ “ነኝ” አይደለም ያለው፡፡ የዚህ ቃል ትርጓሜ ጉዳይ አሳሳቢ ላይሆን ይችላል፤ ማስተከከሉ ግን ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም፡፡

ሌላም አለኝ፡፡ በየአብያተ ክርስቲያናት መድረክ የምንሰማው “የናዝሬቱ ጌታ” የሚል አጠራር ግራ ያጋባኛል፡፡ ምን ማለት ነው? ጌታ ኢየሱስ ናዝራዊ መሆኑን ለማሳየት “የናዝሬቱ ኢየሱስ” መባሉ ትክክል ነው (ማቴ. 2÷23፤ ማር. 14÷67፤ 16÷6፤ ዮሐ. 1÷46)፤ “የናዝሬቱ ጌታ” ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም፡፡ አዎን፤ ጌታ ኢየሱስ የናዝሬትም ጌታ ነው፤ የናዝሬት ጌታ ብቻ ግን አይደለም፡፡ የዓለም ሁሉ ጌታ እንጂ! ስለዚህ ጌታ ኢየሱስን “የናዝሬቱ ጌታ” ብሎ መጥራት የአንድን አገር ፕሬዘዳንት የአንድ ቀበሌ ሊቀ መንበር አድርጎ ከመጥራትም እጅግ እጅግ የከፋ ነው፡፡ አጠራራችን ቢስተካከል ይበጃል፡፡

እስራኤላውያን የሰቀሉትን “ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው” እንድናውቅ ተጽፎልናል (ሥራ 2÷36)፡፡ ታዲያ “ኢየሱስ ክርስቶስ” ወይም “ክርስቶስ ኢየሱስ” ወይም “ጌታ ኢየሱስ” ከማለት ይልቅ “ኢየሱስ” ብቻ ብሎ መጥራት እንዴት ነው የለመድነው? “ኢየሱስ” ብቻ ማለት ምሉዕ አይሆንም፡፡

ሌሎች የእምነት አባቶቻችንንም ስም ስንጠራ አክብሮታችንን በመግለጥና በትህትና ቢሆን ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ጳውሎስን፣ ጴጥሮስንና ሌሎችን ሐዋርያትን በሌጣ ስማቸው ብቻ ከመጥራት ልማድ ብንወጣና “ሐዋርያው (ቅዱስ) ጳውሎስ”፣ “ነቢዩ ሙሴ”፣ “ጠቢቡ (ንጉሡ) ሰለሞን”፣ “ንጉሡ (ቅዱስ) ዳዊት”፣ ቅድስት (ድንግል) ማርያም በማለት ብናከብራቸው ምናለበት!? ምክንያቱም የጳውሎስንና የጴጥሮስን ሐዋርያነት፣ የሙሴን ነቢይነት፣ የዳዊትን ንግሥና፣ የሰለሞንን ጠቢብነት፣ የማርያምን በድንግልና ፅንሳ መውለድ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል፡፡ በተጨማሪም ለሰሚውም ደስ ይላል፡፡ ትህትናንም እንማርበታለን፤ ነቀፌታችንንም በመቀነስ ለወንጌል ሥርጭት የሚያግዝ ሁኔታን መፍጠር እንችላለን፡፡ አይመስላችሁም??

ጌታ ይባርካችሁ

ማስታወሻ

[1]. የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር፤ *አማርኛ መዝገበ ቃላት፤* (አዲስ አበባ፤ 1993 ዓ.ም)፡፡